**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር**

**ለብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ**

**አዲስ አበባ**

ጉዳዩ:- **የኤጀንሲውን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት ይመለከታል፤**

በርዕሱ የተጠቀሰውን ኤጀንሲው የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 24 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 18 ገጽ አባሪ በድምሩ 42 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል። በመሆኑም በገጽ 43 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ

የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች

ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**

**በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር**

**የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ**

# የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

# የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

**ሚያዝያ 2010 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር

## የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ

## የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

### መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

### ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን የኤጀንሲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው፡፡

### የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

### ኦዲታችን የሚያካትተው፡-

- ✓ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- ✓ የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣

- ✓ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል።

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል።

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም።

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን።

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

## <u>የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ሥራ አመራር በ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ የካቲት 13 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር OFAG.F-02.14/4/8 በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መጋቢት 11 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር አ5.1/9 በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1. <u>የገቢ ሂሳብ</u>

#### 1.1. <u>ታሪፍ ሳይኖረው የተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ</u>፤

##### 1.1.1. <u>ግኝት</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 21 መሰረት ኤጀንሲው ለሚሰበስበው ገቢ በመንግሥት የጸደቀ ታሪፍ መኖሩን እና ገቢው በታሪፉ መሰረት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኤጀንሲው በበጀት ዓመቱ ለስቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የአየር ትንቢያ መረጃ ከሰጠበት አገልግሎት ገቢ ብር **1,076,729.31** የሰበሰበ ቢሆንም በሚመለከተው አካል የጸደቀ ታሪፍ ባለመኖሩ ምክንያት ገቢው መሰብሰብ በሚገባው መጠን ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን ስለሁኔታው በ2006፣ በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመታት ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ሳይወሰድ በድጋሚ ተገኝቷል፡፡

##### 1.1.2. <u>ሥጋት</u>

- ታሪፍ ሳይኖር ገቢ መሰብሰብ የአሰራር ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡
- የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓቱን ያዳክማል፡፡
- የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ  አያስችልም፡፡

##### 1.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኤጀንሲው ያለታሪፍ ለሚሰበሰበው ገቢ ታሪፍ አውጥቶ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ማስደረግ እንዳለበት በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

### 1.1.4. የሥራ አመራር ምላሽ

ኤጀንሲው ባቋቋመው ኮሚቴ አማካኝነት ጥናቱ የተጠናቀቀ ሲሆን በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ ከአቬየሽን፣ ከቦሌ ኤርፖርት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አድርጎ ለማስወሰን የስብሰባ ኘሮፖዛል ቀርቧል፡፡

### 1.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ኤጀንሲው አዲስ ታሪፍ የሚያጠና ኮሚቴ አቋቁሞ ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመወያየት ጥረት እያደረገ የሚገኝ በሆንም ሂደቱ መዘግት ይታይበታል፡፡ ስለሆነም እየተሰራበት ባለው ታሪፍ እንዲሰራ እየተደረገ ጎን ለጎን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 21 መሰረት ታሪፉ በሚመለከተው አካል በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲጸድቅ መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

## 2. ተሰብሳቢ ሂሳብ

### 2.1. በደንቡና በመመሪያው መሰረት ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ፤

### 2.1.1. ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ኤጀንሲው በደንቡና በመመሪያው መሰረት የፈጸመ መሆኑ ሲጣራ በተለያዩ የተሰብሳቢ የሂሳብ ኮዶች (መደቦች)፡-

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር **288,441.42**፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር **1,181,951.14**፣
- ከአምስት በላይ እስከ አሥር ዓመት ድረስ የቆየ ብር **1,435,952.77**

በድምሩ ብር 2,906,345.33 በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) ለረዥም ጊዜያት በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን ስለሁኔታው በ2006, በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡
(ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

### 2.1.2. ሥጋት

በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ፡-

- የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል፡፡
- ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡
- የሂሳብ መግለጫውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

### 2.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፤ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ግን በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ፤ በተጨማሪም የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ሁኔታው ተጣርቶ ደንብና መመሪያውን ተከትለው እንዲሰረዙ መደረግ እንዳለበት በድጋሚ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

### 2.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. በ4201 የሂሣብ መደብ ብር 40,707.73 እና በ4203 የሂሣብ መደብ ብር 38,190.29 ባለቤቱ ተለይቶ በሰነድ የሚፈለግባቸውን ሂሣብ እንዲያወራርዱ ጥሪ የተደረገ ቢሆንም በተሰጣቸው ጊዜ ገደብ ቀርበው ባለማወራረዳቸው ከደመወዛቸው 1/3ኛ በየወሩ እየተቀነሰ ገቢ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡
2. በ4201 የሂሣብ መደብ ብር 27,713.62 እና በ4203 የሂሣብ መደብ ብር 269,162.29 በጠቅላላ ብር 296,875.91 ባለቤቱ የተለየ ቢሆንም

በተለያዩ ምክንያት መሥሪያ ቤቱን የለቀቁና በሞት የተለዩ በመሆናቸው ጉዳዩ በህግ እንዲያዝ ለመሥሪያ ቤቱ የህግ ክፍል ከማስረጃ ጋር ተላልፏል።

#### 2.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ያልተወራረዱት ሒሳቦች ሁኔታ ተጣርቶ መወራረድ (መሰብሰብ) የሚችሉት ሂሳቦች እንዲወራረዱ (እንዲሰበሰቡ)፤ መወራረድ (መሰብሰብ) የማይችሉት ሂሳቦች ደግሞ መመሪያውን ተከትለው እንዲዘረዙ መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

## 2.2. መደበኛ የሂሳብ ሚዛኑን ያልጠበቀ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

### 2.2.1. ግኝት

በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ 5/2003 መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳቦች የዴቢት ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከ2008 በጀት ዓመት ወደ 2009 በጀት ዓመት በተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ የዞረው ከወጪ ቀሪ መነሻ ሚዛን (Beginning Balance) የክሬዲት ሚዛን ብር 492,835.78 የሚያሣይ ሲሆን ስለሁኔታው በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ሁኔታው ያልተጣራና የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

### 2.2.2. ሥጋት

ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ሚዛናቸዉን ያልጠበቁ ከሆነ፡-

- ☞ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ በየሒሳብ መደቡ የተመለከቱትን ሂሳቦች ትክለክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ☞ የተዘጋጀውን የሂሳብ ሪፖርት ተአማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።

### 2.2.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል። የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል።

### 2.2.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ሂሳቦችን የማስተካከያ ሂሳብ ሰርተን እርምጃ ወሰደን የምናሳውቃችሁ መሆኑን እንገልፃለን።

### 2.2.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ስለሁኔታው በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድበት በድጋሚ ተገኝቷል። ሆኖም በዚህ በጀት ዓመት ኤጀንሲው ሁኔታው በማጣራት የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የጀመረውን ጥረት በማጠናከር በቀሪዎቹ ሚዛናቸውን ባልጠበቁ ሂሳቦችም ላይ ትኩረት ሰጥቶ ሁኔታው እንዲጣራ በማድረግና በተጨባጭ ማስረጃ በማስደገፍ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

# 3. <u>ተከፋይ ሂሳብ</u>

## 3.1. <u>ለረጅም ጊዜ በተከፋይ የተያዙ ሂሳቦች</u>፤

### 3.1.1. <u>ግኝት</u>

በኤጀንሲው የሚገኙት ተከፋይ ሂሳቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ እንዲሁም መሥሪያ ቤቱ ያለበትን ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኤጀንሲዉ በተለያዩ የተከፋይ ሂሳብ ኮዶች (መደቦች)፡-

- ከአንድ ዓመት በላይ አስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 687,628.09፣
- ከአምስት በላይ አስከ አሥር ዓመት ድረስ የቆየ ብር 558,277.85፣

- ከአሥር ዓመት በላይ የቆየ ብር 739,750.87፣

በድምሩ ብር 1,985,656.81 ሳይከፈል ለረዥም ጊዜያት በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን ስለሁኔታው ከ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም ጀምሮ የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)

### 3.1.2. ሥጋት

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተአማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።

### 3.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ መከፈል ይኖርባቸዋል። ለረጅም ዓመታት ሲንከባለል የመጣውና ለማን እንደሚከፈል የማይታወቀው ተከፋይ ሂሳብ ሁኔታው ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።

### 3.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በ5002 የሂሳብ መደብ ላይ ከዚህ በፊት ይታይ የነበረውን የሰነድ ክምችት ላይ በአብዛኛው የማስተካከያ እርምጃ ተወስዷል። ቀሪው ብር 749,466.05 ኮሚቴ ተቋቁሞ የድርጊት መርሃ ግብር አውጥቶ እየሰራ ይገኛል። በ2010 በጀት ዓመት የማስተካከያ እርምጃ ወስደን ሁኔታውን የምናሳውቅ ይሆናል።
- በ5035 የሂሳብ መደብ የሚታየው ብር 739,750.87 ለረጅም ጊዜ ሲንከባለል የመጣ በመሆኑ ቅድሚያ ተሰጥቶት እየተጣራ በመሆኑ በሰነድ አጣሪ ኮሚቴ ተጣርቶ ወደፊት እርምጃ ይወሰዳል።
- በ5061 የሂሳብ መደብ የሚታየው ብር 496,439.89 የመያዣ ሂሳብ ባለመብቶቹ ተመላሽ እንዲደረግላቸው በወቅቱ ለመሥሪያ ቤቱ ጥያቄ

ያላቀረቡ በመሆኑ ሲሆን፣ ቆየት ያሉትን ከገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር አጥርተን እርምጃ ወስደን የምናሳውቅ ይሆኖል፡፡

### 3.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

መከፈል ያለባቸው ሂሳቦች እንዲከፈሉ፤ መከፈል የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ሁኔታው ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

## 3.2. መደበኛ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ተከፋይ ሂሳቦች፤

### 3.2.1. ግኝት

በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የተከፋይ ሂሳቦች የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከ**2008** በጀት ዓመት ወደ **2009** በጀት ዓመት በተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ የዞረው ከወጪ ቀሪ መነሻ ሚዛን **(Beginning Balance)** በብር **1,577,751.38** ዴቢት ሚዛን የሚያሣይ ሲሆን፣ ስለሁኔታው በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት አስተያት የተሰጠበት ቢሆንም ሁኔታው ያልተጣራና የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

### 3.2.2. ሥጋት

ሂሳቦች መደበኛ የክሬዲት ሚዛናቸዉን ያልጠበቁ ከሆነ፡-

- ☞ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ በየሒሳብ መደቡ የተመለከቱትን ሂሳቦች ትክለክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- ☞ የተዘጋጀውን የሂሳብ ሪፖርት ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

### 3.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡

### 3.2.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የሂሳብ መደባቸውን ያልጠበቁ ተከፋይ ሂሳቦች እየተጣሩ ስለሆነ በሂደት የማስተካከያ እርምጃ ወስደን የምናሳውቅ ይሆናል፡፡

### 3.2.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ስለሁኔታው በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድበት በድጋሚ ተገኝቷል፡፡ ሆኖም በዚህ በጀት ዓመት ኤጀንሲው ሁኔታው በማጣራት የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የጀመረውን ጥረት በማጠናከር በቀሪዎቹ ሚዛናቸውን ባልጠበቁ ሂሳቦችም ላይ ትኩረት ሰጥቶ ሁኔታው እንዲጣራ በማድረግና በተጨባጭ ማስረጃ በማስደገፍ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

# 4. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

## 4.1. <u>አለአግባብ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ</u>፤

### 4.1.1. <u>ግኝት</u>

መሥሪያ ቤቱ የፈጸማቸው የምሳ አበል ክፍያዎች ሰኔ 2004 በወጣው የመንግሥት የቀን ውሎ አበል የአበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኛ የሆኑት አቶ ገዛኸኝ ማሙሻ ለመስክ ስራ ጉዳይ ሁመራ እና ቀብሪደሀር በሄዱበት ወቅት ለሥራ ለቁዩበት 6.2 ቀናት ብቻ ታሳቦ ብር **1,031.78** መከፈል ሲገባው ለ10 ቀናት ብር **1,651.50** በመከፈሉ ምክንያት ከቆዩበት ቀናት በላይ በብልጫ ብር **619.72** የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

(ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል)

### 4.1.2. <u>ሥጋት</u>

- ☞ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ እንዲሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- ☞ ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሣጣው ይችላል፡፡
- ☞ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

#### 4.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

አለአግባብ የተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱ የውሎ አበል ክፍያ መፈጸም ያለበት መንግሥት ያወጣውን የክፍያ መመሪያ ተከትሎ መሆን ይኖርበታል።

#### 4.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

አላአግባብ ብር 619.72 ተከፍሎ የተገኘውን የውሎ አበል ተመላሽ እንዲያደርጉ እርምጃ ወስደን የምንሳውቅ መሆኑን እንገልጻለን።

### 4.2. <u>ያለአግባብ የተከፈለ የዓመት ፈቃድ ክፍያ እና ከዓመት ፍቃድ ላይ ያልተቀነሰ የሥራ ግብር</u>፤

#### 4.2.1. <u>ግኝት</u>

1. በፌዴራል የመንግሥት ሰራተኞች አዋጅ 515/1999 ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 39:-

   - ✓ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሥራው ሁኔታ በማስገደዱ ምክንያት መሥሪያ ቤቱ ለሰራተኛው የዓመት እረፍት ፍቃዱን ሊሰጠው ያልቻለ እንደሆነ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከሁለት የበጀት ዓመት ላልበጠ ጊዜ ሊያስተላልፈው እንደሚችል እና ሆኖም ያልተጠቀመበት የዓመት እረፍት ፍቃድ በሶስተኛው በጀት ዓመት ለሰራተኛው መሰጠት እንዳለበት፤

   - ✓ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 36(3) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የዓመት ፍቃዱ ለሚተላለፍበትና ፍቃዱ በገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጠው ለሚጠይቅ ሰራተኛ በጀት በቅድሚያ በማሲያዝ ከተላለፈው የዓመት ፍቃድ ውስጥ የመጀመሪያውን የአንዱን ዓመት የሥራ ቀናቶች ብቻ በማሰብ በገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጠው መደረግ እንዳለበት፤

ተደንግጓል።

2. በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን በተመለከተ በክፍል ሁለት አንቀጽ 12 በተደነገገው መሰረት እንዲሁም በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነጻ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም (ለምሳሌ የቤት አበል ቦነስ የአመት ፍቃድ ክፍያ የአገልግሎት ካሳ … ወዘተ) ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁና በደንቡ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ ነሐሴ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በቁጥር 1 አውግ-54 በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለሥልጣን አሳዉቋል፡፡

በዚሁ መሰረት ኤጀንሲው ለዓመት እረፍት ሥራ የፈጸመው ክፍያ አግባብነትን እና ከክፍያው ላይ የተቀነሰውን ሥራ ግብር ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በአዋጁ መሰረት የ2007 በጀት ዓመት የአመት ፍቃድ በገንዘብ የተቀየረ ሲሆን የ2008 በጀት ዓመት ፈቃድ ወደ 2010 በጀት ዓመት መዞር ወይም ፍቃዱ ለሰራተኛዉ ፈቃድ መስጠት ሲገባ ያለአግባብ ብር 88,497.60 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
   (ለዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል)

2. ለሰራተኞቹ ከተፈጸመው የዓመት ፈቃድ ክፍያ ላይ ብር 5,684.00 ሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፣ (ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)

በድምሩ ብር 94,181.60 አለአግባብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

### 4.2.2. ሥጋት

- ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- የወጣውን የመንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ተከትሎ ክፍያ ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሣጣው ይችላል፡፡
- ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

### 4.2.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ያለአግባብ የተከፈለዉ የዓመት ፈቃድና ሳይቀነስ የቀረዉ ግብር ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም የዓመት እረፍት ፍቃድ በገንዘብ ሲቀየር በአዋጁ መሰረት መሆን እንዳለበት እናሳስባለን።

### 4.2.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

በ2008 በጀት ዓመት የዓመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጣቸው ለተደረጉ ሠራተኞች ተመላሽ እንዲያደርጉና ለሠራተኞች ከተፈጸመው የዓመት እረፍት ክፍያ ላይ ያልተቀነሰው የስራ ግብር ተቀናሽ በማድረግ እርምጃ ወስድን የምናሳውቃችሁ መሆኑን እንገልፃለን።

### 4.2.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

በማሻሻያ ሃሳቡ በተገለጸው መሰረት ያለአግባብ የተከፈለዉ የዓመት ፈቃድና ሳይቀነስ የቀረዉ የሥራ ግብር ተመላሽ እንዲደረግ እንዲሁም ለወደፊቱ የዓመት እረፍት ፍቃድ በገንዘብ ሲቀየር በአዋጁ መሰረት መሆን እንዳለበት እናሳስባለን።

## 4.3. <u>ከስራ ለለቀቁ ሰራተኛ የተከፈለ ደመወዝ</u>፤

### 4.3.1. <u>ግኝት</u>

በተለያየ ወቅት ለተቀጠሩና ኤጀንሲዉን ለለቀቁ ሰራተኞች የተፈጸመው የደመወዝ ክፍያ ሰራተኞቹ በሥራ ላይ ለነበሩበት ጊዜ ብቻ መሆኑን ለማጣራት በናሙና ኦዲት ሲደረግ አንድ ሰራተኛ ከስራ ከለቀቁ በኋላ ያልሰሩበት ደመወዝ ብር 414.33 የተከፈላቸው መሆኑ ታውቋል።

(ለዝርዝሩ አባሪ 7 ተያይዟል)

### 4.3.2. <u>ሥጋት</u>

- የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ እንዲሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል።

### 4.3.3. የማሻሻያ ሃሳብ

አለአግባብ ለሠራተኞች የተከፈለው ደመወዝ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም ሰራተኛ ሲለቅ የደመወዝ ክፍያ እንዳይፈጸም የሰው ሀብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በወቅቱ ለፋይናንስ ክፍሉ ማሳወቅ ይኖርበታል። ሂሳብ ክፍሉም አለአግባብ ክፍያ እንዳይፈጸም ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

### 4.3.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የወ/ሮ እመቤት ተስፋዬ የመጋቢት ወር ደመወዝ ክፍያ ከተከፈለ በኃላ ከሰዉ ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ከስራ መልቀቃቸዉን ሚያዝያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም ለፋይናንስ የስራ ክፍል የደረሰ በመሆኑ አለአግባብ የተከፈላቸዉ ደመወዝ ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊዉን እንፈጽማለን።

### 4.3.5. የኦዲተሩ አስተያየት

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 12(1ሀ) መሰረት ለደመወዝ ዝግጅት ሊሟሉ ከሚገባቸው መረጃዎች ውስጥ አንዱ የመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች የክፍሉ ሰራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። የሥራ ክፍሎቹ ይህንን መረጃ ወር በገባ በ20ኛው ቀን የፋይናንስ ተግባርን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል በግልባጭም የአስተዳደር ተግባርን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል ማሳወቅ እንዳለባቸው ተመልክቷል።

በመሆኑም ኤጀንሲው ይህንን አሰራር ተግባራዊ ባለማድረጉ ያለአግባብ የደመወዝ ክፍያ ሊፈጸም ችሏል። ስለሆነም በቀጣይ የሥራ ክፍሎቹ በመመሪያው መሰረት ሰራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን ሊያሳውቁ ይገባል። አለአግባብ የተፈጸመው ክፍያም ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል።

## 5. በቅ/ጽ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ላይ የታዩ ክፍተቶች፤

### 5.1. አለአግባብ የተፈጸመ የአበል ክፍያ፤

#### 5.1.1. ግኝት

የአዳማ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል የፈጸማቸዉ የስልጠናና ሌሎች የዉሎ አበል ክፍያዎች ሰኔ 2004 ዓ.ም የወጣዉን የመንግሥት ሰራተኞች የአገር ዉስጥ የቀን ዉሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት በማድረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዳማ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል በኩል ለመካከለኛ አመራር፤ ለሰዉ ሀብት ስራ አመራር እንዲሁም ለመልካም አስተዳደር ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና በቢሾፍቱ ከተማ ፒራሚድ ሆቴል እና ሪዞርት ከመጋቢት 2 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ መጋቢት 4 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ለሶስት ቀናት ሥልጠና የተዘጋጀ ሲሆን በስልጠና ወቅት ለምሳ ወጪ ለሆቴሉ ክፍያ ተፈጽሞ እያለ በተጨማሪ የውሎ አበል ክፍያ ብር 10,259.00 የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 8 ተያይዟል)

#### 5.1.2. ሥጋት

- የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ እንዲሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሣጣው ይችላል።
- ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል።

#### 5.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

አለአግባብ የተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጠር ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል።

#### 5.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ለሆቴሉ የተከፈለዉ የ3 ቀን በመሆኑ ያለአግባብ የተከፈለው የምሳ አበል ትክክል ባለመሆኑ ለወደፊቱ የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን።

#### 5.1.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ያለአግባብ የተፈጸመዉ ክፍያ የምሳ አበል ተመላሽ ሊደረግ ይገባል። ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጠር ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

### 5.2. <u>በሂሳብ አመዘጋገብ ሥርዓቱ ላይ የታዩ ክፍተቶች</u>፤

#### 5.2.1. <u>ግኝት</u>

የአዳማ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል የፋይናንስ የአሰራር ሥርዓት አግባብነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በናሙና ከታዩት የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች ውስጥ አልፎ አልፎ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች ላይ ቀን የማይጻፍ መሆኑ፣
2. ሰራተኞች ለስራ በሚወጡበት ወቅት የውሎ አበል ክፍያ ሲፈፀም የመንግስት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ እና የዉሎ አበል ማወራረጃ ቅጹ በትክክል የማይሞላ መሆኑ (በፋይናንስ ብቻ የሚሞላ የቀን ብዛትና የዉሉ አበል መጠን አልፎ አልፎ የማይሞላ መሆኑ)፣
3. ማዕከሉ በፋይናንስ ሥርዓቱ መሰረት ለተሰብሳቢና ለተከፋይ ሂሳቦች ሌጀር ያልተዘጋጀ እና ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርቱም ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን ያላካተተና የተሟላ ያለመሆኑ፣

ታውቋል።

#### 5.2.2. <u>ሥጋት</u>

ማዕከሉ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ክፍተት ሊፈጥር እንዲሁም ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋትና ለጉድለት መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል።

#### 5.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ማዕከሉ ከላይ የታዩትን የውስጥ ቁጥጥር አሰራር ክፍተቶች በመፈተሽ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ፤ ኤጀንሲውም ተገቢውን ሥልጠናና እገዛ በማድረግ የተሟላ የሂሳብ ሪፖርት እንዲቀርብ መደረግ ይኖርበታል።

#### 5.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ከላይ በዝርዝር በኦዲቱ የተገለጹት ግኝቶች ትክክል ስለሆኑ ወደፊት የምናስተካክል መሆኑን እናረጋግጣለን።

## 6. ንብረት

### 6.1. የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድን በተመለከተ፤

#### 6.1.1. ግኝት

የኤጀንሲው የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፦

1. **በኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት**

   - የሜትዎሮሎጂ ዕቃዎች አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ በኮንቴነር ዉስጥ ተቀላቅለዉ እና ተከማችተዉ የሚገኙ መሆኑ፣
   - ለተቆጠሩት ቋሚ ዕቃዎች ማመዛዘኛ ያልተሰራላቸዉ መሆኑ፣
   - የተቆጠሩት ቋሚ ዕቃዎች ከስቶክ ካርድና ከተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card ) ከተመለከተው ጋር የማስታረቅና የማመሳከር ሥራ ያልተሰራ ከመሆኑም በተጨማሪም በተጠቃሚዎች እጅ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ንብረቶች የተዘጋጀው መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) በተጠቃሚዉ ያልተፈረመ መሆኑ፣

- በኤጀንሲዉ ዋና መሥሪያ ቤት፣ በአዳማና በአዋሳ ማዕከሎች ሰራተኞች ለሚጠቀሙባቸዉ የቀጥታ ስልክ መስመሮች በሥራ አመራሩ የተቀመጠ/የተወሰነ ጣሪያ የሌለ መሆኑ፣

2. <u>በአዳማ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል</u>

4. የተበላሹ 7 ኮምፒዉተሮች፣ 2 የፎቶ ኮፒ ማሽኖች እና ብዛት ያላቸዉ አሮጌ የመኪና ጎማዎች በንብረት ክፍል የሚገኙ መሆኑ፣

5. የማዕከሉ አላቂና ቋሚ ዓመታዊ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ማመዛዘኛ ያልተሰራለት መሆኑ እና ያልተሰራባቸዉ የሂሳብ ደረሰኞች ዓመታዊ ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፣

6. ድንገተኛ የእሳት መከላከያ በተለያዩ ቢሮዎች አካባቢ ቢኖርም ለረዥም ዓመታት በባለሙያ ባለመፈተሹ ምክንያት አገልግሎት መስጠት/አለመስጠቱ የማይታወቅ መሆኑ፣

7. አልፎ አልፎ ከዋናዉ መሥሪያ ቤት ለማዕከሉ የሚላኩ ደረሰኞች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የማይደረጉ መሆኑ፣

3. <u>በሀዋሳ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል</u>

- ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች የተሟላ መመዝገቢያና መቆጣጠሪያ የሚሆን ስቶክ ካርድ እየተሠራበት ያለመሆኑ፣

- የግምጃ ቤት ሠራተኛው ቢን ካርድ፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ምዝገባን ደርበው የሚሰሩ መሆኑ፣

- በመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል (ጎፋም) መሰረት በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) በሁለት ቅጅ ተዘጋጅቶ አንዱ ለተጠቃሚው ሌላው በንብረት ክፍል እንዲያዝ ያዛል። ይሁን እንጂ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/የሚቲ/አገልግሎት ማዕከል ንብረት ክፍል በተሟላ ሁኔታ የማይሰራበት መሆኑ፣

- ከዋናው መሥሪያ ቤት ለተላኩ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኞች (ሞዴል19) ያልተቆረጠላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ለንብረት ገቢና ወጪ እንዲሁም ለገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ቆጠራ ያልተደረገላቸው መሆኑ፣
- በንብረት ክፍል ዉስጥ የተለያዩ አይነት ዕቃዎች መወገድ ሲገባቸዉ ሳይወገዱ በግምጃ ቤት ተከማችተዉ የሚገኙ መሆኑ፣ (ለምሳሌ የመኪና ጎማዎች ብዛት 80 ፣ ሼልፍ ብዛት 15፣ ዲስክ ቶፕ ኮምፒውተሮች ብዛት 6 ፣ ሞኒተር ኮምፒውተሮች ብዛት 4 እና የመሳሰሉት ይገኙበታል)
- ግምጃ ቤቱ የእሳት አደጋ ጊዜ መከላኪያ የሌለው መሆኑ፣

ታዉቋል፡፡

### 6.1.2. ሥጋት

- ኤጀንሲው መንግሥት ባወጣዉ የንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መሰረት የማይፈጸም ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ስርዓት መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- የመንግሥት ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- የቋሚ ንብረት ቆጠራ በመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል (ጎፋም) መሰረት ካልተከናወነ እንዲሁም የቆጠራው ውጤት እንዲታወቅ ካልተደረገ የመንግሥት የሀብት አጠቃቀም፣ አጠባበቅና አያያዝ ሥርዓቱን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባው ይችላል፡፡

### 6.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኤጀንሲዉ በመንግሥት ንብረት አስተዳደርና አያያዝ መመሪያ መሰረት የታዩት ክፍተቶች እንዲስተካከሉ፤ መወገድ ያለባቸው ንብረቶች እንዲወገዱ፤ ከዚህም በተጨማሪ የኤጀንሲውና የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከሎች ሰራተኞች ለሚጠቀሙባቸዉ የቀጥታ ስልክ ቁጥሮች በኤጀንሲው ሥራ አመራር የክፍያ ጣሪያ እንዲወሰን መደረግ ይኖርበታል፡፡

## 6.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

### 1. በዋናው መሥሪያ ቤት

- ✓ በኮንቴነር ዉስጥ አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ተቀላቅለዉ የሚገኙ የሚቲዎሮሎጂ እቃዎች በአይሲቲ (ICT) ዳይሬክቶሬት ስር የሚገኙ ባለሙያዎች ለስራቸዉ የሚጠቀሙባቸዉና የዳይሬክቶሬቱ ንብረቶች ናቸዉ። ስለሆነም የሚሠሩትን ከማይሠሩት ለይተዉ እንዲያስቀምጡ የተነገራቸው ስለሆነ ክትትል በማድረግ እዲስተካከል እናደርጋለን።
- ✓ የቋሚ እቃዎች ቆጠራ ማመዛዘኛ ያልተሠራላቸዉ በመሆኑ ወደፊት ለመስራት በእንቅስቃሴ ላይ ያለን መሆኑን እናሳዉቃለን።
- ✓ የተጠቃሚዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (UC) ቀደም ሲል በክፍሉ በነበረዉ የሰዉ ኃይል እጥረት ምክንያት የተወሰኑ ስራዎች ያልተሠሩ መሆኑን ታይቷል። በቀጣይ የተሰጡ አስተያየቶችን ወስደን እንሰራለን።
- ✓ ኤጀንሲዉ ለሚጠቀምባቸዉ የቀጥታ መስመር ስልኮች ከዚህ ቀደም ቦሌ በነበርን ሰዓት በህንጻዉ መሰነጣጠቅ ምክንያት ስልኮቻችን ሁሉም  በሚባል ደረጃ አይሰሩም ነበር። ነገር ግን አሁን ጥቁር አንበሳ ስንገባ የቀጥታ መስመር ለገባላቸዉ ክፍሎች ጣሪያ ለማዉጣት በበላይ አመራሩ ኮሚቴ ተዋቅሮ እየሠራ ይገኛል።

### 2. በአዳማ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል

ከላይ በዝርዝር በኦዲት የተገለጹት ግኝቶች ትክክል ስለሆኑ ወደፊት የምናስተካክል መሆኑን እናረጋግጣለን።

### 3. በሀዋሳ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል

- ✓ ስቶክ ካርድ ምዝገባ ያለመካሄዱ ስህተት ነው። ነገር ግን ወደ ፊት የምንሰራበትና የምናስተካክል ይሆናል።

- ✓ የቋሚ ዕቃ ምዝገባ ሰራተኛ እና የንብረት ቁጥጥር ሠራተኛ የተሟላ ስላልሆነ የዕቃ ግምጃ ቤት ሰራተኛ ስራውን ደርበው እየሰሩ በመሆኑ ወደ ፊት ሠራተኛ በቅጥር ሲሟላ የሚስተካከል ይሆናል።
- ✓ የዩዘር ካርድ ምዝገባ ያልተካሄደ ስለሆነ ወደፊት አስፈላጊውን ክትትል አድርገን የሚፈጸም ይሆናል።
- ✓ አንድ የቀጥታ ገቢ ደረሰኝና አንድ የቅድሚያ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኝ ከዋናው መሥሪያ ቤት መጥቶ ገቢ ያለመደረጉ ስህተት ነው። ይሁን እንጂ በቆጠራ ጊዜ ያልተቆጠረበት ምክንያት ሰነዶቹ በስራ ላይ ስላሉ ነው።
- ✓ ንብረት ማስወገድ ማዕከሉ ሥልጣን ስለሌለው ንብረቱ ግን እንዲወገድ በቆጠራ ጊዜ ለሚመለከተው ክፍል ያሳወቅን ሲሆን ወደ ፊት ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ችግሩን የምንፈታ መሆኑን እንገልፃለን።
- ✓ በወቅቱ የነበረው የእሳት አደጋ ማጥፊያ ጊዜው ያለፈበት ስለሆነ ወደ ፊት እቃውን የምናሟላና የምናስተካክል ይሆናል።

### 6.1.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ከላይ ለግኝቶቹ በተሰጠው ምላሽ መሰረት የተጀመሩ ሥራዎች የንብረት አስተዳደር መመሪያውን ተከትለው ተጠናክረው መቀጠል ያለባቸው ሲሆን ሊስተካከሉና በንብረት አስተዳደር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥሩ የሚችሉ ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቷቸው በአስቸኳይ እንዲስተካከሉ መደረግ እንዳለባቸው ለማሳሰብ እንወዳለን።

## 7. በጀት

### 7.1. በሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ሂሳብ፤

#### 7.1.1. ግኝት

ለኤጀንሲዉ ለ2009 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የመደበኛና የካፒታል የወጪ በጀት በሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ፡-

- ከመደበኛ በጀት ብር 4,625,772.15፤
- ከካፒታል በጀት ብር 11,366,385.57 በድምሩ ብር 15,992,157.72 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 9 ተያይዟል)

#### 7.1.2. ሥጋት

የወጪ ሂሣብ በጀቱ በእቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል።

#### 7.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኤጀንሲው የበጀት ዕጥረት ካጋጠመው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትሎ የበጀት ዝውውር መጠየቅ ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በጎላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

#### 7.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ስለተራፊው በጀት ለተሰጠው ምላሽ አባሪ 10 ተያይዟል።

#### 7.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ኤጀንሲዉ በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል። በተጨማሪም መሥሪያ ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙ ላይ ክትትል በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት

የበጀት እጥረት ላለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

## 8. ልዩ ልዩ

### 8.1. ዋስትና በሚያስፈልጋቸዉ የስራ መደቦች ላይ የተመደቡ ሰራተኞች ዋስትና (ተያዥ) እንዲያቀርቡ ያልተደረገ ስለመሆኑ፤

#### 8.1.1. ግኝት

በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 ተራ ቁጥር 6(1) መሰረት በገንዘብ ያዥነት፣ በንብረት ያዥነትና ጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲያቀርቡ ያዛል። ሆኖም በናሙና የተመረጡት ሰራተኞች የግል ማኅደራቸው ሲታይ በሀዋሳ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል የጥበቃ ሰራተኛ የሆኑት አቶ ዳዊት ቱቡሉ፣ አቶ በየነ ወዳጆ ፣ አቶ ባራና ባሌ፣ አለማየሁ ከበደ፣ አቶ እሸቱ ኤጃሞና ፍስሃ ግዛቸዉ የተባሉ ሰራተኞች ዋስትና (ተያዥ) እንዲያቀርቡ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል።

#### 8.1.2. ሥጋት

በገንዘብ ያዥነት፣ በንብረት ያዥነትና ጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሠራተኞች ላይ ለሚደርሰው ጥፋት ተጠያቂ እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል።

#### 8.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በገንዘብ ያዥነት፣ በንብረት ያዥነትና በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሠራተኞች በመመሪያው መሰረት ዋስ እንዲያቀርቡ በተጨማሪም ሌሎች ዋስ ያላቀረቡ ሰራተኞች ሊኖሩ ስለሚችሉ ሁኔታው ተጣርቶ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል።

## 8.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የተጠቀሱት ሠራተኞች ከሚሰሩበት የሥራ ክፍል ኃላፊነት አንጻር ዋስትና እንዲያቀርቡ የመንግሥት መመሪያ በመጥቀስ በማስታወቂያ ቢጠየቅም ከሁለት ሠራተኞች በስተቀር ሌሎቹ ሳይቀርቡ ቀርተዋል። በቀጣይ መመሪያውን ተከትለን እነዚህ ሠራተኞች የንብረት ክፍል ሠራተኛውን ጨምሮ ዋስትና እንዲያቀርቡ ካላቀረቡ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚወሰድ በማስታወቂያ በመግለጽ የማስተካከል ሥራ እንሰራለን።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በኤጀንሲው ኃላፊዎችና ሰራተኞች ስለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን።

አባሪ. 1

**<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ የቆይታ ጊዜ ዝርዝር</u>፤**

| ተራ ቁጥር | የሂሳብ መደብ ቁጥር | የተሰብሳቢ ሂሳቡ ክፍያ የተፈጸመበት ጊዜ | የቆይታው ጊዜ | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ | ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ | ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት ድረስ የቆየ | |
| **1.** | 4201 | ከ2003 እስከ 2009 በጀት ድረስ | **1,868.96** | **451,610.75** | **64,228.76** | **517,708.47** |
| **2.** | 4203 | ከ1997 እስከ 2009 በጀት ድረስ | | | **495,793.05** | **495,793.05** |
| **3.** | 4210 | ከ2000 እስከ 2009 በጀት ድረስ | | **640,241.79** | **570,680.41** | **1,210,922.20** |
| **4.** | 4211 | ከ1998 እስከ 2009 በጀት ድረስ | **3,596.29** | **44,931.84** | **34,058.22** | **82,586.35** |
| **5.** | 4254 | ከ1999 እስከ 2009 በጀት ድረስ | **282,976.17** | | **3,817.46** | **286,793.63** |
| **6.** | 4273 | ከ1997 እስከ 2009 በጀት ድረስ | | **2,312.93** | **20,456.39** | **22,769.32** |
| **7.** | 4274 | ከ1997 እስከ 2009 በጀት ድረስ | | **42,853.83** | **246,918.48** | **289,772.31** |
| | | **ድምር** | **288,441.42** | **1,181,951.14** | **1,435,952.77** | **2,906,345.33** |

**አባሪ. 2**

**መደበኛ የሂሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦች ዝርዝር ፡**

| ሂሳብ መደብ | ተሰብሳቢ ሂሳብ ሐምሌ 1,2008 ዓ.ም | | ተከፋይ ሂሳብ ሐምሌ1,2008 ዓ.ም | |
|---|---|---|---|---|
| | ዴቢት | በክሬዲት | ዴቢት | በክሬዲት |
| **4201** | | 74,132.22 | | |
| **4203** | | 92,372.70 | | |
| **4210** | | 22,803.98 | | |
| **4211** | | 19,992.40 | | |
| **4251** | | 22,589.26 | | |
| **4254** | | 1,098.15 | | |
| **4273** | | 2,668.37 | | |
| **4274** | | 257,178.70 | | |
| **5002** | | | 493,723.65 | |
| **5003** | | | 751,657.35 | |
| **5004** | | | 332,370.38 | |
| **ድምር** | | **492,835.78** | **1,577,751.38** | |

**አባሪ. 3**

<u>የተከፋይ ሒሳብን የቆይታ ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር</u>

| ተራ ቁጥር | የሂሳብ መደብ ቁጥር | ተከፋይ ሂሳቡ የተያዘበት ጊዜ | የቆይታው ጊዜ | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ | ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ | ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት ድረስ የቆየ | ከአስር ዓመት በላይ የቆየ | |
| **1.** | **5002** | ከ2002 እስከ 2009 በጀት ድረስ | | **687,628.09** | **61,837.96** | | **749,466.05** |
| **2.** | **5035** | ከ1997 እስከ 2009 በጀት ድረስ | | | | **739,750.87** | **739,750.87** |
| **3.** | **5061** | ከ1999 እስከ 2009 በጀት ድረስ | | | **496,439.89** | | **496,439.89** |
| ድምር | | | | **687,628.09** | **558,277.85** | **739,750.87** | **1,985,656.81** |

አባሪ. 4

**<u>ለአቶ ገዛኸኝ ማሙሻ በብልጫ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ፣</u>**

| ምዝገባ የተከናወነበት ቀን | የወጪ ቫውቸር ቁጥር | የተከፈለው የገንዘብ መጠን | ለመስክ ሥራ የሄዱበት ቦታ | በአውሮፕላን የጉዞ ትኬት መሰረት | | የቆየበት ቀን | ሊከፈል የሚገባው የውሎ አበል | የተከፈለ የውሎ | በብልጫ የተከፈለ የውሎ አበል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወደ መስክ የሄዱበት | ከጉዞ የተመለሱበት | | | | |
| 30/05/09 | 1020477 | 3,490.00 | ሁመራ | **16/01/17 (08/05/09)** | **19/01/17 (11/05/09)** | **3.6** | **622.80** | **173*5=865.00** | **242.20** |
| | | | ቀብሪ ደሀር | **23/01/17 (15/05/09)** | **25/01/17 (17/05/09)** | **2.6** | **408.98** | **157.30*=786.50** | **377.52** |
| **ድምር** | | | | | | | **1,031.78** | **1,651.50** | **619.72** |

**<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-**

**የቀብሪደሀር የቀን የውሎ አበል የበረሀ አበልን ይጨምራል፡፡**

**አባሪ. 5**

<u>አዋጁን ሳይከተል በገንዘብ የተቀየረ የ2008 በጀት ዓመት የዓመት ፍቃድ ዝርዝር ፤</u>

| ተራ ቁጥር | የሰራተኛዉ ስም | የተከፈለዉ የዓመት ፈቃድ | የተከፈላቸዉ የዓመት ፈቃድ ቀናት | የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Fetene Teshome | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 13,598.00 |
| 2 | Dula shanko | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 12,037.00 |
| 3 | Mehiret Mulugta | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 7,647.00 |
| 4 | Lisan Ayele | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 5,901.00 |
| 5 | Mulatu Debebe | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 6,036.00 |
| 6 | Genet Lakew | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 3,740.00 |
| 7 | Lemlerm Mohammed | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 3,278.00 |
| 8 | Birhanu Dejene | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 6,809.00 |
| 9 | Belachew Kebede | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 5,333.00 |
| 10 | Melak Dessie | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 4,867.00 |
| 11 | Getachew Tesgaw | የ2008 በጀት ዓመት | 28 | 5,633.60 |
| 12 | Amarch Tilahun | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 6,809.00 |
| 13 | Saba Ayalew | የ2008 በጀት ዓመት | 30 | 6,809.00 |
| **ጠቅላላ ድምር** | | | | **88,497.60** |

## የ2007 በጀት ዓመት የዓመት እረፍት በገንዘብ ሲቀየር ከክፍያው ላይ ያልተቀነሰ ሥራ ግብር ዝርዝር፤

| ተራ ቁጥር | የሰራተኛ ስም | ወርሃዊ ደመወዝ | የዓመት ፈቃድ ብዛት | በገንዘብ የተቀየረ የዓመት ፍቃድ | የጠቅላላ ክፍያው ድምር | ከጠቅላላ ክፍያው ላይ መቀነስ ያለበት የሥራ ግብር | ከወርሃዊ ደመወዝ ላይ የተቀነሰ ሥራ ግብር | ከዓመት እረፍት ክፍያ ላይ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | መቀነስ ያለበት የሥራ ግብር (4-5) | ሥራ ግብር ተቀንሶ የተፈጸመ ክፍያ | ሥራ ግብር ተቀንሶ መፈጸም ያለበት ክፍያ (3-6) | ያልተቀነሰ የሥራ ግብር |
| | | 1 | 2 | 3 | 1+3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 7-8 |
| 1 | Tsegaye Ketema | 9,714.00 | 26 | 8,418.80 | 18,132.80 | 4,846.48 | 1,959.20 | 2,887.28 | 5,596.28 | 5,531.52 | 64.76 |
| 2 | Kassahune Zewudie | 9,714.00 | 28 | 9,066.40 | 18,780.40 | 5,073.14 | 1,959.20 | 3,113.94 | 5,984.84 | 5,952.46 | 32.38 |
| 3 | Mehiret Mulugta | 7,647.00 | 18 | 4,588.20 | 12,235.20 | 2,782.32 | 1,346.75 | 1,435.57 | 3,405.42 | 3,152.63 | 252.79 |
| 4 | Tafesse Regassa | 9,714.00 | 17 | 5,504.60 | 15,218.60 | 3,826.51 | 1,959.20 | 1,867.31 | 3,962.53 | 3,637.29 | 325.24 |
| 5 | Gentu Eskziyaw | 6,809.00 | 26 | 5,901.13 | 12,710.13 | 2,948.55 | 1,137.25 | 1,811.30 | 4,180.62 | 4,089.83 | 90.79 |
| 6 | Haymanot Amsalu | 7,647.00 | 19 | 4,843.10 | 12,490.10 | 2,871.54 | 1,346.75 | 1,524.79 | 3,558.36 | 3,318.31 | 240.05 |
| 7 | Amedin Abdulkerm | 9,177.00 | 26 | 7,953.40 | 17,130.40 | 4,495.64 | 1,798.10 | 2,697.54 | 5,317.04 | 5,255.86 | 61.18 |
| 8 | Chali Debele | 7,443.00 | 26 | 6,450.60 | 13,893.60 | 3,362.76 | 1,295.75 | 2,067.01 | 4,482.83 | 4,383.59 | 99.24 |
| 9 | Yoseph Wubtaye | 6,361.00 | 8 | 1,696.27 | 8,057.27 | 1,462.18 | 1,025.25 | 436.93 | 1,432.20 | 1,259.34 | 172.86 |
| 10 | Henok Hailu | 5,420.00 | 23 | 4,155.33 | 9,575.33 | 1,917.60 | 790.00 | 1,127.60 | 3,145.70 | 3,027.73 | 117.97 |
| 11 | Kidest Mekonen | 4,269.00 | 22 | 3,130.60 | 7,399.60 | 1,284.90 | 551.30 | 733.60 | 2,457.39 | 2,397.00 | 60.39 |
| 12 | Lishan Ayele | 6,809.00 | 26 | 5,901.13 | 12,710.13 | 2,948.55 | 1,137.25 | 1,811.30 | 4,180.62 | 4,089.83 | 90.79 |
| 13 | Mulatu Debebe | 6,036.00 | 19 | 3,822.80 | 9,858.80 | 2,002.64 | 944.00 | 1,058.64 | 2,938.46 | 2,764.16 | 174.30 |
| 14 | Genet Lakew | 3,740.00 | 18.5 | 2,306.33 | 6,046.33 | 946.58 | 445.50 | 501.08 | 1,889.75 | 1,805.25 | 84.50 |
| 15 | Lemlem Mahamed | 3,278.00 | 19.5 | 2,130.70 | 5,408.70 | 787.18 | 353.10 | 434.08 | 1,758.03 | 1,696.62 | 61.41 |
| 16 | Tesfahun Admasu | 3,278.00 | 28.5 | 3,114.10 | 6,392.10 | 1,033.03 | 353.10 | 679.90 | 2,446.67 | 2,434.20 | 12.47 |
| 17 | Tamiru Tadesse | 6,809.00 | 25 | 5,674.17 | 12,483.17 | 2,869.11 | 1,137.25 | 1,731.86 | 4,055.79 | 3,942.31 | 113.48 |
| 18 | Tebeletse Tekle | 6,809.00 | 24 | 5,447.20 | 12,256.20 | 2,789.67 | 1,137.25 | 1,652.42 | 3,930.96 | 3,794.78 | 136.18 |
| 19 | Kassahun H/mariam | 2,872.00 | 29 | 2,776.27 | 5,648.27 | 847.07 | 288.30 | 558.77 | 2,227.07 | 2,217.50 | 9.57 |
| 20 | Taye Assefa | 5,304.00 | 7.5 | 1,326.00 | 6,630.00 | 1,092.50 | 761.00 | 331.50 | 1,143.30 | 994.50 | 148.80 |
| 21 | Tibebu Assefa | 2,628.00 | 23 | 2,014.80 | 4,642.80 | 626.06 | 251.70 | 374.36 | 1,671.10 | 1,640.44 | 30.66 |
